COLORADO

Department of Labor and Employment

This is an Amharic translation of the Colorado Overtime and Minimum Pay Standards (“COMPS”) Order poster.
For more information or for another language, call 303-318-8441.

# COMPS ሕግ #36 ፖስተር

## የኮሎራዲ የትርፍ ጊዜ እና የዝቅተኛ ክፍያ መስፈርት ሕግ

**የስራ ክፍል መስፈርቶች እና ስታቲስቲክስ**
**ተፈጻሚ የሚሆነው ማርች 16፣ 2020 (መጋቢት 7 2012)**

### ዝቅተኛ ደመወዝ በኮሎራዶ፡ በሰዓት $12፣ ወይም $8.98 ጉርሻ ለሚያገኙ ሰራተኞች፣ ከ 1/1/2020 (ታኅሣሥ 22 2012 ዓ.ም) ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል።

- ዝቅተኛ ደመወዝ በየዓመቱ በዋጋ ግሽበት ተስተካክሎ፤ የቀጣዩ ዓመት COMPS እና ፖስተር የ2021ዱን **(2012 ዓ.ም)** ዝቅተኛ ደመወዝ ይሰጣል።
- ዝቅተኛ ደመወዝ፣ በ COMPS መተዳደሪያ አንቀጽ 2 የታገዱ ካልሆነ በስተቀር፣ በሰዓትም ይሁን በሌላ መልኩ (ደመወዛቸው፣ ኮሚሽን፣ በተወሰነ ስራ ወዘተ) የሚከፈላቸው በሁሉም አዋቂዎች እና ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ በሆኑ ለአካለ መጠን ያልደረሱ ልጆች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። ከሞግዚት አስተዳደር ነጻ ያልሆነ ለአካለመጠን ያልደረሰ ልጅ ከዝቅተኛው በ15% ያነሰ ሊከፈለው ይችላል።
- የፌደራል ዝቅተኛ ክፍያ ($7.25) እና ሌሎች (ከ1/1/20)\ ጀምሮ የዴንቨር $12.85ን) ጨምሮ ሁሉም ማንኛውም የክልሉ ዝቅተኛ ክፍያዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላል።
  ስራው በተደራራቢ የዝቅተኛ እና ተጨማሪ ሰዓት ህጎች የተሸፈነ ከሆነ፣ ለከፍተኛ ደመወዝ ወይም መስፈርት የወጣው ህግ ተፈጻሚ ይሆናል።

### ተጨማሪ ሰዓት፡ በሳምንት ከ40 ሰዓታት እና በቀን ከ12 ወይም ከተከታታይ 12 ሰዓታት በላይ ሲሆን ክፍያው ከመደበኛው የክፍያ መጠን በ1 ½ ተጨማሪ ይሆናል።

- ከሁለት እና ከዚያ በላይ ሳምንታት በላይ ያለፉ ሰዓታት ተጨማሪ ሰዓትን ለማስላት በአማካይ አይወሰዱም።
- አሰሪዎች በተጨማሪ ጊዜ ሰዓት እና በግማሽ የትርፍ ሰዓት ክፍያ ምትክ የእረፍት ጊዜ (በተለምዶ መጠሪያው “comp time”) መስጠት አይችሉም።

### የመመገቢያ ሰዓታት፡ ከ5 ሰዓት በላይ ለሆኑ ፈረቃዎች ለ30 ደቂቃዎች ያልተቆራረጠ እና ከስራ ነጻ የሆነ ጊዜ።

- ሰራተኞች ክፍያ በማይፈጸምበት የመመገቢያ ሰዓታቸው ከሁሉም አይነት ስራዎች ነጻ መሆን እና የግል ተግባራቸውን ለማከናወን ሊፈቀድላቸው ይገባል።
- ስራው ያልተቆራረጠ የመመገቢያ ጊዜ እንዲኖር የማያመች በሚሆንበት ጊዜ፣ በስራ ወቅት መመገብ ሊፈቀድ ይገባል፤ ለጊዜውም ክፍያ ሊከፈል ይገባል።
- በተቻለ መጠን፣ የመመገቢያ ሰዓቶች በትንሹ የስራ ፈረቃው ከጀመረ ከ1 ሰዓት በኋላ እና ከማለቁ ከአንድ ሰዓት በፊት መሆን አለባቸው።

### የእረፍት ጊዜያት፡ ክፍያ የሚፈጸምባቸው በየ4 ሰዓቱ ለ10 ደቂቃ የሚሰጡ።

| #የስራ ሰዓቶች፡ | እስከ 2 | >2, እስከ 6 | >6, እስከ 10 | >10, እስከ 14 | >14, እስከ 18 | >18, እስከ 22 | >22 |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| #የእረፍት ሰዓቶች | 0 | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 |

- የእረፍት ሰዓቶች ከስራ ቦታ ውጪ መሆን የለባቸውም፣ ነገር ግን ስራን ሊያካትቱ አይገባም፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን ሁሉ በየ4 ሰዓታት መካከል ላይ መሆን አለባቸው።
- እረፍት በትክክል የሚወሰድበት ሁኔታ፣ ያለምንም ጫና ተቀጣሪዎች እና ቀጣሪዎች በፈቃደኝነት ሲስማሙ፣ እና 5 ደቂቃ ወደ መጸዳጃ ቤት ወይም ሌላ ቦታ ሄዶ ለመመለስ በቂ በሚሆንበት ጊዜ በአንድ ሙሉ 10 ደቂቃ ምትክ ሁለት 5 ደቂቃ እረፍት ጊዜዎች ሊፈቀዱ ይችላሉ። ለግብርና ፣ ለቤት ሕክምና እንክብካቤ ሰጪዎች እና ለጋራ ድርድር የስራ አይነት አመቺ እንዲሆን ተጨማሪ የ5 ደቂቃ ጊዜ ይሰጣል።
- የእረፍት ጊዜን የማያስከብሩ እና የማይፈቅዱ አሰሪዎች የእረፍት ጊዜ መሆን ለነበረበት ነገር ግን ስራ ለተሰራበት ተጨማሪ የስራ ሰዓት ክፍያ ሊከፍሉ ይገባል።

### የተሰራበት ሰዓት፡ አሰሪዎች ለራሳቸው ጠቀሜታ ለስራ/አገልግሎት አፈጻጸም ብለው የሚመድቡት ሰዓት ሊከፈል ይገባል።

- በሁሉም ጊዜያት በቅጥር ግቢዎች ውስጥ፣ በስራ ላይ ወይም በተመደቡበት የስራ ቦታ ያሉ (ከስራ ውጪ ያሉ ሰራተኞችን ግቢ ውስጥ ሲሆኑ ማለት አይደለም)፣ በተጨማሪ
  - የስራ ልብሳቸውን/መከላከያ የሚለብሱ ወይም የሚያወልቁ (ከስራ ወጪ የሆኑ የሚለበሱ ልብሶችን አይጨምርም)፣ በመጸዳዳት/ በመዘጋጀት ላይ ወይም ሌሎች ከስራ ሰዓት ውጪ ያሉ ስራዎችን የሚሰሩ፤
  - በስራ ቦታቸው ትዕዛዝን፣ ወይም ከስራ ጋር የተያያዘ መረጃን መቀበል ወይም ለመጋራት የሚጠባበቁ
  - የጥበቃ/ደህንነት ፍተሻ፣ መግቢያ እና መውጫ ሰዓት ሲሆኑ መያዝ/ሲሆኑመመልከት፤ ወይም
  - ከላይ ያሉትን ስራዎች የሚጠባበቁ።
- ለአሰሪው ጥቅም የሚደረግ ጉዞ የስራ ሰዓት ነው፤ መደበኛ የቤት/የስራ ጉዞ አይካተትም።
- የጉዞ ሰዓት እና የመኝታ ሰዓት ላይ በተጨማሪ አንቀጽ 1.9.2ን ይመልከቱ።

### ተቀናሾች፣ ብድር እና ከደመወዝ ተቀናሽ ክፍያዎች በ C.R.S ስር ያሉ ገደቦች ተፈጻሚ ናቸው። 8-4-105 እና ቀጥሎ

- በሰዓት እስከ $3.02 የሚደርሱ የጉርሻ ብድሮች (ዝቅተኛ ደሞዝን ወደ $8.98 ዝቅ በማድረግ) በመደበኛ፣ በአሰራር ከ$30 በላይ በጉርሻ ለሚያገኙ ይፈቅዳሉ። የሰዓት ክፍያው እና ጉርሻው ተደምሮ ከሙሉ ዝቅተኛ ደመወዙ በታች ከሆነ፣ አሰሪው ልዩነቱን ሊከፍል ይገባል።
- በፈቃደኝነት ተቀባይነት ላገኙ ምግቦች (የአሰሪውን ትፍር ሳይጨምር) ዋጋ ወይም ክፍያ የመመገቢያ ብድሮች ይፈቅዳሉ።
- ለማረፊያ የሚደረጉ ተቀናሾች ሊፈቀዱ የሚችሉት በሰራተኛው በገዛ ፈቃዱ ተቀባይነት ያገኙ ሲሆኑ፣ በቀዳሚነት ለሰራተኛው ጥቅም (ለአሰሪው ሳይሆን) በጽሁፍ ሲቀርቡ እና እንደ ቤቱ አይነት እስከ $25 ወይም $100 ድረስ በሳምንት የተወሰኑ በሚሆኑበት ጊዜ ነው።
- በልዩ ቁስ ወይም ቅርጽ ያልተሰሩ መደበኛ አልባሳት የሆኑ የደንብ ልብሶች ግዴታ ሊቀርቡ አይገባም፤ ሌሎች የደንብ ልብሶች ያለምንም ወጪ ሊቀርብ ይገባል። አሰሪዎች አስፈላጊ ለሆነ ማንኛውም እጥበት ሊከፍሉ ይገባል፤ ለተለመደ እርጅና እና መቀደድ ተቀማጭ ወይም ተቀናሽ መጠየቅ አይችሉም።

### ከ COMPS ሕጎች ውስጥ ከግዴታ ነጻ የሚደረጉ፤ አጠቃላይ አንቀጽ 2 ስር የተዘረዘሩት፤ ዋናዎቹ ተቀናሾች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል።

- አመራሮች/ተቆጣጣሪዎች፣ ውሳኔ ሰጪ የአስተዳደር ሰራተኞች፣ እና ባለሙያዎች (አንቀጽ 22. 1-3) ከግዴታ ነጻ የሆነ ደመወዝ ይከፈላቸዋል።

| ደመወዝ እስከ 6/20 | 7/20-12/20 | 2021 | 2022 | 2023 | 2024 | ከ2024 በኋላ ያሉት እያንዳንዱ አመታት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ቢያንስ ለሁሉም ሰዓታት ከዝቅተኛ ክፍያው ጋር እኩል የሆነ | $35,568 | $40,500 | $45,000 | $50,000 | $55,000 | የበፊቱ ዓመት ደመወዝ፣ የዋጋ ግሽበት ተስተካክሎ |

- 20% የሚሆኑት ባለንብረቶች ወይም በመንግስታዊ ያልሆኑት ውስጥ ያሉ ከፍተኛ ክፍያ/ ከፍተኛ-ደረጃ ያላቸው ሰራተኞች፣ ወደ አስተዳደር ስራ ውስጥ ከገቡ (2.2.5)።
- ከኮምፒውተር ጋር የተገናኘ ከፍተኛ የቴክኒክ ሰራተኞች (በ2.2.10 ስር ትርጓሜ የተሰጣቸው) ሆነው በዶላር በሰዓት ዝቅተኛ $27.63 የሚከፈላቸው ከሆነ።
- በርካታ በቤት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች፣ ንብረት አስተዳዳሪዎች፣ የ ሬንጅ ሰራተኞች እና የካምፕ/የውጪ ላይ ትምህርት የመስክ ሰራተኞች (2.2.7) ።
- ሁሉም ባይሆኑም፣ በርካታ የሽያጭ ሰራተኞች (2.2.4፣ 2.4.1፣ 2.4.2) እና የትራንስፖርት ሰራተኞች (2.2.6)።
- የተወሰኑ የሕክምና ትራንስፖርት እና የሆስፒታል/የቤት ነርስ አገልግሎት ሰራተኞች ለየት ያሉ የተጨማሪ ሰዓት ህጎች አሏቸው (2.4.4፣ 2.4.5)
- ተራራ መውረድ ሸርተቴ/የበረዶ መንሸራተት ሰራተኞች፣ ማረፊያን ሳይጨምር፣ በተራራ ላይ ምግብን አካቶ ከ40 ሰዓት የትርፍ ሰዓት ክፍያ ግዴታ ነጻ ናቸው (2.4.3)።
- የግብርና ስራዎች ከተጨማሪ ሰዓት እና የመመገቢያ ሰዓት ግዴታ ነጻ ናቸው፣ የእረፍት ጊዜያትን በተመለከተ ነጻነት አላቸው (2.3)።

### ቅሬታዎች እና በቀል ተከላካይ መብቶች

- የስራ ክፍፍል መስፈርቶች እና ስታቲስቲክስ (የመገኛ አድራሻ በዚህ ፖስተር ከላይ ይገኛል) በፌደራል፣ በክልል ወይም በአካባቢው ሕግ ስር የተቀመጡ ያልተከፈለ ዝቅተኛ ወይም የስራ ሰዓት ውጪ ክፍያን ቅሬታዎች ይቀበላሉ። እንደ አማራጭ ሰራተኞች በፍርድ ቤት ክስ ማቅረብ ይችላሉ።
- ያልተከፈለ ክፍያን በተመለከተ ሀላፊነት ያለባቸው አካላት በስራቸው የአንድ ተቋም አሰሪን፣ እና በተቋሙ የተግባር ላይ ቁጥጥር የሚያደርጉ ግለሰቦችን ያካትታሉ።
- አሰሪዎች የተፈጠረን ወይም የሚጠበቅን የክፍያ ማጣራት፣ ችሎት፣ ቅሬታ ወይም የክርክር አጸፋን ለመመለስ፣ ጣልቃ ለመግባት፣ ወይም ለመጣስ ሲሉ፣ በማስፈራራት መበቀል፣ ማስገደድ ወይም አድልዎ መፈጸም አይችሉም።
- የክፍያ ጥሰት ወይም የበቀል መከላከል ጉዳዮች ለክፍሉ እንደ ቅሬታ ወይም ሚስጥራዊ ጥቆማ ሊቀርቡ ይችላሉ።

### የ COMPS ሕግ ፖስተርን መለጠፍ እና ትርጉም

- መለጠፍ፡ አሰሪዎች ይህንን ፖስተር ሰራተኞች በስራ ቀን በቀላሉ ሊያነቡት በሚችሉበት ቦታ ማሳየት ይኖርባቸዋል። በአካል መለጠፍ የማይቻል ከሆነ፣ አሰሪዎች የፖስተሩን ኮፒዎች ወይም የ COMPS ሕግን ለእያንዳንዱ ሰራተኛ በመጀመሪያ የስራ ወር ውስጥ መስጠት አለባቸው።
- ስርጭት፡ አሰሪዎች በተጠየቁ ጊዜ ይህንን ፖስተር፣ እና ቅጂውን ከማንኛውም የተጻፈ መመሪያ ወይም ፖሊሲ ጋር በማድረግ ሊያቀርቡ ይገባል፣
- ትርጉም፡ ሰራተኞች ውሱን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው ከሆነ እና ስፓኒሽ የሚናገሩ ከሆነ አሰሪዎች ይህንን ፖስተር በስፓኒሽ መለጠፍ አለባቸው። ሰራተኞቹ ከስፓኒሽ ውጪ ሌላ ቋንቋ የሚናገሩ ከሆነ፣ አሰሪው በዛ ቋንቋ የተሰራ ፖስተር ከክፍሉ መጠየቅ አለበት።

**ፖስተሩ ሁሉንም ባይሆንም፣ በ COMPS ሕግ ስር ያሉ ቁልፍ የክፍያ ሕጎችን አጠቃሎ ይይዛል፣ በተጨማሪ የክፍያ ሕጉን ሙሉ መረጃዎችን ይዟል ተብሎ ሊወሰድ አይገባም።**
**ሙሉ የ COMPS ሕግን እና ሌሎች የክፍያ ህግ መረጃዎችን ለማግኘት፣ ወይም ለክፍያ ህግ ጥያቄዎች፣ አድራሻ፡**
**የስራ ክፍል መስፈርቶች እና ስታቲስቲክስ፣ coloradolaborlaw.gov, cdle_labor_standards@state.co.us, 303-318-8441 / 888-390-7936.**